


በፕሬዘደንት
ዲየትር ኤፍ ኡክዶርፍ
የቀዳሚ አመራር
ሁለተኛ አማካሪ

# አጠቃላይ ጉባኤ—ልዩ የሆነ በረከት

አንድ ጥሩ የቤተክርስቲያን አባል የእኛ እምነት አባል ካልሆነ ጎረቤት ጋር ይነጋገር ነበር። የንግግር ርዕሱ ወደ አጠቃላይ ጉባኤ ሲቀየር፣ ጎረቤቱ እንዲህ ጠየቀ፣ “ነቢያት እና ሐዋሪያት አሉን ትላለህ? በአመት ሁለት ጊዜም በአለም አቀፍ ጉባኤ የእግዚአብሔርን ቃል ይገልጻሉ?”

አባሉም በልበሙሉነት “ያለጥርጣሬ” ብሎ መለሰ።

ጎረቤቱም ስለዚህ ለትንሽ ጊዜ አሰበ። በቅንነት ለአወቅ የሚፈልግ ይመስል ነበር እና ከእዚያም፣ “ባለፈው የአጠቃላይ ጉባኤ ምን አሉ? ብሎ ጠየቀ።”

በዚህ ጊዜ ጥሩው የቤተክርስቲያኗ አባል ስሜታ ወንጌሉን ለመካፈው ከመደሰት ወደ እፍረት ስሜታ ተቀየረ። በምንም ቢሞክር፣ የአንድ ንግግርን ዝርዝር ለማስታወስ አልቻለም።

ጓደኛው ይህም እንዲረበሽ አደረገው እና እንዲህ አለ፣ “እግዚአብሔር ለሰው ይናገራም እናም አንተ ምን እንዳለ አታስታውስል ትነኛለህ?”

ይህ ወንድምም በዚህ ንግግር ትህትና ተሰማው። በአጠቃላይ ጉባኤ በጌታ አገልጋዮች የሚናአገሩትን ቃላት ለማስትወስ ቃል ገባ።

እያንዳንዱን የአጠቃላይ ጉባኤ ለማስታወስ የሚያስሸግር እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን፣ እናም ሁሉንም ለማስታወስ ስለማንችል ማፈር አያስፈገንም። ይህም ቢሆን፣ በእያንዳንዱ አጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ እንደ ስጦታ እና ከሰማይ ለግል የህይወት ጉዳያችን እንደ በረከት የሚሰጡ መልእክቶች አሉ።

ለአጠቃላይ ጉባኤ ለመዘጋጀት፣ በጌታ አገልጋይ የሚንነገሩንን ቃላት ለመቀበል፣ ለማስታወስ፣ እና ፤እመጠቀም የሚረዱን ሶስት መሰረታዊ መመሪያዎችን በሀሳብ ላቅርብ።

### 1. በአጠቃላይ ጉባኤ የሚነገሩትን ቃላይ ሲያዳምጡ እና ስይስጠኑ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኗ አባላት ለግል ራዕይ መብት አላቸው።

ለአጠቃላይ ጉባኤ ስትዘጋጁ፣ መልስ ለማግኘት የምትፈልጓቸውን እንድታሰላስሉ እጋብዛችኋለሁ። ለምሳሌ፣ ፈተና በሚያጋጥማችሁ ነገሮች ላይ የጌታን መመሪያ ለማግኘት ትፈልጉ ይሆናል።

ለጸሎታችሁ መልስ በቀጥታ ከአንድ ንግግር ወይም ከአንድ ሀረግ ሊመጣ ይችላል። በሌሎች ጊዜዎችም መልሶች የሚገናኙበት በማይታይ ቃል፣ ሀረግ፣ ወይም መዝሙር በኩል ሊመጣም ይችላል። በህይወት በረከቶች የተሞላ እና የምክር ቃላትን ለማዳመጥ እና ለከመተል ጥብቅ ፍላጎት ያለው ልብ ለግል ራዕይ መንገድን ያዘጋጃል።

### 2. መልእክቱ በፊት የምታውቁት ቢመስልም ችላ አትበሉት።

ነቢያት ሁልጊዜም የሚያስተምሩት በመደጋገም ነው፤ ይህም የመማር ህግ ነው። በአጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ የሚደጋገሙ ጭብጥ መልእክቶች እና ትምህርቶችን ትሰማላችሁ። ማረጋገጫ ልስጣሁ፥ ይህ አዲስ ነገሮችን ለመፍጠር በአይነ

ህሊና የማይት ችሎታ ስላጡ አይደለም። ወደ ሌሎች ነገሮች ከመሄዳችን በፊት መገባት እና መደረግ የሚያስፈልጋቸው ታላቅ ዘለአለማዊ ነገሮችን መሰረታዊ መመሪያ በአዕምሮአችን እና በልባችን ላይ ለማስተኮር እና ለማስተማር ጌታ በመፈለጉ ምክንያት ነው በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ መልእክቶችን ለማዳመጥ የምንቀጥለው። ጥበባዊ ገንቢ ግድግዳውን እና ጣራውን ከመስራቱ በፊት መጀመሪያ መሰረቱን ይመሰርታል።

**3. በአጠዋላይ ጉባኤ የሚናገሩት ቃላት በሚቀጥሉት ወሮች መንገድን የሚያመለክቱን የአቅጣጫ መለያ መሳሪያችን ሊሆኑ ይገባቸውል።**

የመንፈስ መነሳሻን ካዳመጥን እና ከተከተልን፣ ወደፊታችን ያሉትን ሸለቆዎች እና ተራራዎች በመቋቋም፣ በማይታወቀው ውስጥ መርተውን እንደምናልፍበት ሊያሆና ያገለግሉናል፣ (1 ኔፊ 16 ተመልከቱ)

አለም ከተፈጠረች ጊዜ ጀምሮ፣ እግዚአብሔር ለጊዜአቸ ሀዎች የሰማይን ፍላጎት የሚናገሩ ነቢያት ጠርቷል። ማዳመጥ እና ከእዚያም ጌታ የሰጠንን መልእክቶች የመጠቀም ሀላፊነት የእኛ ነው።

ምህሪውና አፍቃሪው የሰማይ አባታችን ልጁቹን አልካደም እናም አይክዳቸውም። ዛሬ፣ እንደ ድሮም፣ ሐዋሪያትን እና ነቢያትን መድቧል። ቃላቱን ለእነርሱ መግለጥን ቀጥሏል።

በአጠቃላይ ጉባኤ ለእያንዳንዳችን ያለውን የእግዚአብሔር መልእክት ለመስማት የምንችልበት ምን አይነት አስደናቂ አድል ነው። በአገልጋዮቹ ለሚመጣው ለዚህ ታላቅ በረከት ለሆነው መለኮታዊ መመሪያ እራሳችንን እናዘጋጅ።

ይህም ልዩ የሆነ በረከት ነውና።

---

**ከዚህ መልእክት ማስተማር።**

- አንቅጹን አብራችሁ አንብቡ። ቤተሰብ በአጠቃላይ ጉባኤ ሊያዳምጡ የሚፈልጉትን እንዲያስቡብዳቸው አበረታቷቸው።
- በፕሬዘደንት ኡክዶርፍ የተሰጡትን ምክሮች ትንሽ ልጆች እንዲጠቀሙበት ለመርዳት፣ የአጠቃላይ ጉባኤ መዝገብን አሳዩአቸው (ይህም በጉባኤ በሚታተመው *ሊያሆና* ውስጥ ይገኛል) ቀዳሚ አመራር እን የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን በአጠቃላይ ጉባኤ እንደሚናገሩ አሳውቋቸው። ልጆች ጉባኤን እንዲያዳምጡ እና የተማሩትን እንዲያስታውሱ እንዲረዳቸው ስዕል እንዲስሉ አበረታቷቸው። ወላጆች ልጆች ለማድረግ ለሚችሏቸው ነገሮች conferencegames.lds.org ይጎበኙ።

## ወጣቶች

# ጥሩ፣ የተሻለ፣ ምርጥ

**በሜሪ-ሰለስት ልውስ**

በጥቅምት 2007 (እ.አ.አ) የአጠቃላይ ጉባኤ ንግግራቸው፣ የአስራ ሁለት ሐዋሪያት ቡድን አባል ካህን ዳለን ኤች ኦክስ “ጥሩ፣ የተሻለ፣ እና ምርጥ” ስለሆኑ ተሳታፊ ስለሚደረጉበት ነገሮች ተናገሩ። “ልጆችን ከሚችሉት በላይ ቀጠሮ ስለማድረግ” በሚናገሩበት ጊዜ፣ በተቀመጥኩበት በጥፋተኛነት ስሜታ መስመስመስ ጀመርኩኝ።

ብዛ እያደርግሁኝ እንደሆንኩኝ አውቀው ነበር። በትምህርት ቤት ድራማ ተስታፊ፣ የሚያስቸግሩ ክፍሎችን በትምህርት ቤት የምወስድ፣ እና በተለያዩ ሌሎች ስራዎች ተሳታፊ ነበርኩኝ። የወጣት ሴቶች ስብሰባን በየጊዜው እሳተፍበት ነበር፣ እናም እሁዶቼም የመጨረሻ የትምህርት ስራዎቼን ለመጨረስ የታገልበት ጊዜ ነበር። ሙዚቃን መለማመድ እና የትምህርት ቤትን ጋዜጣ ማረም የሚያስደስቱ ሳይሆን ስራዎች ሆነው ነበር።

የካህን ኦክስ ንግግር ቀጠሮዬን በትኩረት እንድመለከት አደረገኝ። የምሳተፍባቸው ጥሩ ነበር፣ ነገር ግን በጣም ብዙ ነበሩ። ከሁሉም ምርጥ የሚሆነውን መምረጥ ነበረብኝ። ከምሳተፍበት መካከል የትኛውን እንደምተው ለመወሰን ሳስብ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለማንም ሰው ከሁሉም ይበልጥ ጠቃሚ እንደሆነ ገባኝ። ጸሎትን እና ቅዱስ መጻህፍትን ማንበብ ከዘረዘርኳቸው ነገሮች በላይ አደረግኳቸው፣ እናም ከእዚያም ጊዜ ጀምሮ፣ ህይወቴ ያለችግር ይሄድ ነበር።

ካህን ኦክስ ጌታ እንድናደርግ የሚፈልገንን *መጀመሪያ* በመጀመሪያ ስናደርግ፣ ሁሉም ነገሮች በቦታቸው በቀጥታ እንደሚገቡ አስተማሩኝ። ከመጫወቴ በፊት ወይም የቤት ስራን ከመስራቴ በፊት ቅዱሳት መጻህፍቴን ካጠናሁ፣ አስፈላጊ የሆነው ነገር በሙሉ ይከናወናል። እርሱን በሃላ በማሰብ ወደ ህይወቴ ከመጨመር ይልቅ ህይወቴን በጌታ ላይ ስመሰርት፣ ህይወቴ ተጨማሪ ሰላም እና ውጤታማነት አለው።

አሁን በአጠቃላይ ጉባኤ የሚሰጠውን ምክር በጥብቅ አዳምጣለሁ።

## ልጆች

# መልሶችን በአጠቃላይ ጉባኤ ለማግኘት እችላለሁ

ፕሬዘደንት ኡክዶርፍ እንዲህ አስተምረዋል፣ ከአጠቃላይ ጉባኤ በፊት አንዳንድ ጥያቄዎች ካሰባችሁ፣ ጌታ በአጠቃላይ ጉባኤ በነቢያቱ እና በሐዋሪያቱ በኩል ያነጋግራችኋል።

1. እንደ ቤተሰብ እና ክፍል፣ በግለሰብም ይሁን አብራችሁ ምን መማር የሚያስፈልጋችሁን ተወያዩበት። (ለምሳሌ፥ ምስክሬን እንዴት ለማጠናከር እችላለሁ? በትምህርት ቤት ባሉኝ ችግሮች እንዴት ለመቋቋም እችላለሁ?) በወረቀት ላይ ወይም በማስታ ወሻችሁ ላይ ጥያቄዎቻችሁን ጻፉ።
2. ከጉባኤው ከሳምንቶች በፊት ፣ ስለእነዚህ ጥያቄዎች ለማሰብና ለመጸለይ ትችላላችሁ።
3. በጉባኤም ጊዜ ቨጥንቃቄ አዳምጡ (ማስታወሻ መጻፍም ይረዳል)። ከእዚያም ጌታ—በቤተክርስቲያኗ መሪዎች በኩል—እንዴት ጥያቄዎቻችሁን እንደመለሰ ጻፉ።
4. በሌላ ወረቀት ላይ የተማራችሁትን ስታደርጉ የሚያሳይ ስዕለመ ሳል ትችላላችሁ።

© 2011 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩኤስኤ ውስጥ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/10 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/10 (እ.አ.አ)
*First Presidency Message, September 2011* (እ.አ.አ) Ahmaric 09769 506

እምነት • ቤተሰብ • እርዳታ

# መስፈሳዊነትን በማሳደግ ቤተሰቦችን ማጠናከር

*ይህን መዝገብ አጥኑ እና ተገቢ ከሆነ ከምትጎበኟቸው እህቶች ጋር ተወያዩት። እህቶቻችሁን ለማጠናከር እና የሴቶች መረዳጃ ማህበርን የህይወታችሁ ተሳታፊ ክፍል እንዲሆን እንዲረዳችሁ ጥያቄዎቹን ተጠቀሙባቸው።*

የሴቶች መረዳጃ ማህበር አጠቃላይ ፕሬዘደንት ጁሊ ቢ ቤክ እንዳሉት፥ "በውስጤ ስለእግዚአብሔር ሴት ልጆች ዋጋ የሚያጥለቀልቅ ምስክር አድጓል። . . . ከዚህ በላይ ሆኖ የሚያስፈልግ የእምነት እና የግል ጻድቃዊነት ማሳደግ እንዳልነበረ ይሰማኛል። ከዚህ በላይ ሆኖ በጣም የሚያስፈልግ ጠንካራ ቤተሰቦች እና ቤቶች አልነበሩም።"

እህቶች የግል ራዕያቸውን ሲጠቀሙ ጠንካራ ቤት እና ቤተሰብ ለመስራት ለመርዳት ይችላሉ። እህት ቤክም እንዲህ ቀጠሉ፣ "ለግል ራዕይ ብቁ መሆን፣ ይህን መቀበል፣ እናም መጠቀም በእዚህ ህይወት ለማግኘት ከሚችሉት ችሎታዎች ሁሉ በላይ በጣም" አስፈላጊ የሆነው ነው። "ለጌታ መንፈስ ብቁ መሆን የሚጀምረው ለእዚያ መንፈስ ፍላጎት ሲኖር ነው እና ይህም የብቁነት ደረጃን ያመለክታል። ትእዛዛትን ማክበር፣ ንስሀ መግባት፣ እና በጥምቀት የተገቡትን ቃል ኪዳኖች ማሳደስ የጌታ መንፈስ ከእኛ ጋር ሁልጊዜ እንዲገኝ ወደሚያደርግ በረከት ይመራል። ወደ ቤተመቅደስ ቃል ኪዳን መግባት እና ማክበርም የመንፈስ ጥንካሬን እና ሀይልን ወደ ሴት ህይወት ይጨምራል። ለአስቸጋሪ ጥያቄዎች መልስ የሚገኙት ቅዱሳት መጻህፍትን በማንበብ ነው ምክንያቱም ቅዱሳት መጻህፍት የራዕይ ረጂ ናቸውና። . . . በየቀን መጸለይም የጌታ መንፈስ ከእኛ ጋር እንዲሆን ለማድረግ አስፈላጊ ነው።"[1]

የቤተሰብ አባሎቻችን የሰማይ አባትን ዘለአለማዊ አላማ እንዲገባቸው በማድረግ በመንፈስ ለማጠናከር እንችላለን። "ልጆቻችንን ለዘለአለማዊ ሀላፊነቶች በመንፈሳዊነት ለማዘጋጀት ምን ማድረግ እንችላለን?" ብለው የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል ሽማግሌ ኤም ራስል ባለርድ ጠየቁ። "ምናልባት ሁሉንም የሚሸፍን መልስ ቢኖር፥ በወንጌል መሰረታዊ መመሪያዎች እንዴት እንዲሚኖሩ ማስተማር ነው።" ይህም ትምህርት የሚመጣው በየቀኑ በመጸለይ፣ ቅዱሳት መጻህፍትን በማንበብ፣ እና አብሮ እንደ ቤተሰብ በመመገብ፣ በቤተሰብ የቤት ምሽትና በቤተክርስቲያን በመሳተፍ ነው። ሽማግሌ ባለርድ እንደገለጹት፥ "በእያንዳንዱ ቀን፣ አሁንም፣ ለዘለአለም ህይወት እንዘጋጃለን። ለዘለአለም ህይወት ካል ተዘጋጀን፣ ከዚህ በታች ለሚሆን ነገር፣ ምናልባትም ከዚህ በጣም ለሚያንስ ነገር እንዘጋጃለኝ።"[2]

## *ከቅዱስ መጻህፍት*

ምሳሌ 22:6; 1 ዮሀንስ 3:22; ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 11:13–14; 19:38; 68:25

## *ከታሪካችን*

በሚያዝያ 1842 (እ.አ.አ) የሴቶች መረዳጃ ማህበር ስብሰባ ውስጥ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እህቶችን የእራሳቸውን ደህንነት የመፈለግ ጥብቅ ሀላፊነት እንዳላቸው አስተማራቸው። እንዲህም አለ፣ "ከማስተምራችሁ በኋላ፣ ለእራሳችሁ ሀጢያት ሀላፊ ትሆናላችሁ፤ በሰማይ አባታችን ፊት እራሳችሁን ለማዳን እንዲህ መራመዳችሁ የሚያስፈልግ ክብር ነው፤ በጌታችን እራሳችንን ለማዳን እንዲያስችለን የሚሰጠንን ብርሀን እና ጥበብ ለምናሻሽልበት መንገድ ሁላችንም ሀላፊዎች ነን።"[3] ጻድቅ ግለሰቦች እንዲሆኑ፣ ቅዱስ ህዝቦች እንድሆኑ፣ እና ለቤተሰብ ስነስርዓቶችና ቃል ኪዳኖች እንዲዘጋጁ አስተማራቸው።

ማስታወሻዎች

1. ጁሊ ቢ ቤክ፣ "ደግሞም በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፣" *Liahona*፣ ግንቦት 2010፣ 10፣ 11
2. ኤም ራስል ባለርድ, "Spiritual Development፣" *Ensign*፣ ህዳር 1978፣ 65፣ 66
3. የቤተክርስትያኗ ፕሬዘደንቶች ትምህርቶች፤ ጆሴፍ ስሚዝ [2007 (እ.አ.አ)]፣ 355።

### *ምን ማድረግ እችላለሁ?*

**1.** እህቶቼን በመንፈስ እራሳቸውን እንዲህሉ ለመርዳት እንዴት እችላለሁ?

**2.** መንፈስ ቅዱስን ለማወቅ እና መልስ ለመስጠት ያለኝን ችሎታ እንዴት ለማሳደግ እችላለሁ?

ለተጨማሪ መረጃ ወደ www.reliefsociety.lds.org ሂዱ።

© 2011 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩኤስኤ ውስጥ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/10 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/10 (እ.አ.አ) *Visiting Teaching Message, September 2011* ትርጉም Ahmaric 09769 506